ማህበረሰብ

ግንዛቤ ማስጨበጫ
ትምህርት
ማሕበረሰብን የመድረስ ስራ
አቅምን ማዳበር
ክትትል
ምላሽ ሰጪ
እርስ በርሳችን መማማር . . .

የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አልዛይመር፣ዲሜንሽያ የስራ ክፍል ዘርፈ ብዙ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የደህንነት ማስጠበቂያ ስራ በእነዚህ ረገድ ማለትም ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አልዛይመር፣ዲመንሽያ ባሉት ትምህርት ለኤምሲፒዲ ኦፊሰሮች፣ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ ማህበረሰብ እና ግለሰቦች አገልግሎት ይሰጣል። ዓላማው የኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)፣አልዛይመር፣ ዴመንሽያ ያለባቸው ሰዎች ጥሩ ሕይወት ለመኖር የሚያስችላቸው ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ጥሩ ግንዛቤ ያለው ማሕበረሰብን መፍጠር ነው። የስራ ክፍሉ ከቤት ለሚጠፉ እና እርቀው የሚሄዱ ሰዎችን በተመለከተ ለቤተሰብ አባላት እና እንክብካቤ ሰጪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል።

ይህን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፣ **www.montgomerycountymd.gov/aidd**
ወይም ለተጨማሪ መረጃ የፕሮግራም አስተባባሪዎችን ያነጋግሩ።


ሞንትጎመሪ ካዉንቲ፣ ሜሪላንድ • የፖሊስ ዲፓርትመንት
https://www.montgomerycountymd.gov/pol/howdol/autism-alzheimer-outreach.html
ኦፊሰር ሎሪ ሬየስ፣, Laurie.Reyes@montgomerycountymd.gov • (240) 855-1605
ኦፊሰር ታራ ቦንድ፣, Tara.Bond@montgomerycountymd.gov • (240) 671-7498
ኦፊሰር ኤሚ ስቶውተን, Amy.Stoughton@montgomerycountymd.gov • (240) 907-9869


ጁላይ 2024

@mcpnews — መረጃ ለማግኘት ስካን ያድርጉ — mcpnews

የሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ
## የፖሊስ ዲፓርትመንት



# የኦቲዝም፣ የአእምሮ እና የእድገት እክሎች፣ የአልዛይመር፣ የዴመንሽያ የስራ ክፍል

የደሕንነት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በትምህርት፣ ማሕበረሰብን የማንቃት እንዲሁም ስራዎች በመስራት ማስተማር፣የማብቃት፣ የመከታተል እና ምላሽ የመስጠት ስራዎች እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች በ “ባለ ብዙ ዘርፍ/Layered Approach” በሆነው ፕሮግራማችን በኩል አገልግሎት ይሰጣል።

# ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አልዛይመር
## ከቤት የመጥፋትን አደጋ ለመከላከል የደህንነት ምክሮች

- ✓ **ወደ 911 ለመደወል እንዳያመነቱ፣ ሳይቆዩ ቶሎ ይደውሉ።** አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቦች  ወደ 911 ለእርዳታ መደወል እንደማይችሉ ስለሚሰማቸው የጠፋትን ቤተሰቦቻቸውን ብቻቸውን ይፈልጋሉ። ከመኖሪያ ቅጥር ውጭ እየፈለጉ ከሆነ ወደ 911 ይደውሉ። ከደወሉ በኋላ ቤተሰብዎ ወዲያው ከተገኙ ወደ እኛ መልሰው በመደወል ያሳውቁን። ሞንትጎመሪ ካዉንቲ ፖሊስ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አልዛይመር ያለባቸው እና ለአደጋ የተጋለጡ ግለሰቦችን በተመለከተ በሳምንት ከሶስት እስከ አምስት የስልክ ጥሪዎች ይደርሱታል። የቤተሰብ አባላትዎን በቤትዎ በሰላም ለመጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት አንዳንድ ጊዜ በአስቸጋሪ ሁኔታው ውስጥ የሚያልፉት እርስዎ ብቻ አይደሉም። ወደ 911 ቶሎ አለመደወል አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል። ወደ 911 ሲደውሉ የስልክ ጥሪውን ለሚቀበሉት ግለሰብ እና ለአደጋው ምላሽ ለሚሰጡ ፖሊሶች መረጃ ለመስጠት እንዲችሉ "የጹሑፍ" መረጃ ያዘጋጁ። ኦቲዝም ያለባቸው የቤተሰብ አባልዎ ወደ ውሃ አካላት የመሄድ ዝንባሌ ካላቸው ፣ እባኮትን ለ 911 ኦፐሬተር አሳውቁ።

- ✓ **የሆነ አይነት የማሳወቂያ አላርም ያዘጋጁ።** ብዙ ጊዜ እንክብካቤ አድራጊዎች የቤተሰቡ አባል ከቤት መውጣታቸውን ላያውቁ ይችላሉ። በተለይም አመሻሽ ላይ "ጸሃይ ከጠለቀች በኃላ"(ማታ ላይ የሚደረግ የእግር ጉዞ) ሊከሰት የሚችል የተለመደ ነገር ነው። ቀን ላይ የእንክብካቤ ሰጪዎች በሌላ ስራ በሚጠመዱበት ጊዜ አላርም መኖሩ ጥሩ ነው። በባለሙያ የሚገጠም አላርም ማድረግ ካልቻሉ፣ በር ላይ የሚገጠም የማግኔት አላርም ጥሩ አማራጭ ነው። ይህም ውድ ያልሆነ እና ቶሎ የሚገኝ ነው። ይህም አላርም በጠንካራ ፕላስተር ወይም በብሎን በማንኛውም የበሩ ጠርዝ ላይ ሊጣበቅ ይችላል። የተያያዙት ሲላቀቁ (በሩ ሲከፈት) በጣም ጎልቶ የሚሰማ ድምጽ ያወጣል። በር ተደጋግሞ የሚከፈት ከሆነ ከበር ደውል ጋር ማገናኘት ይቻላል።

- ✓ ***መለያ/መታወቂያ*** የቤተሰብ አባልዎን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም መለያ ሁሌም አብሯቸው እንዲሆን ያድርጉ። የቤተሰብ አባሉ የሚገኙበትን የመገኛ አድራሻ መረጃ በማይለቅ ቀለም በልብሳቸው ላይ መጻፍ ጥሩ እና ቀላሉ መንገድ ነው። ነገር ግን፣ የመታወቂያ ዘለበት ተመራጭ መንገድ ነው፣ የጎማ ወይም የሲሊከን (silicone)የተሰሩት የተሻሉ አማራጭ ናቸው። የኤምሲፒዲ (MCPD) እንክብካቤ ሰጭዎች እና ኦቲዝም ያላቸው ግለሰቦች ቤተሰቦች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ዘለበቱን ያደረገው ሰው ዘለበቱን ለፖሊሶች እንዲያሳይ እንዲያደርጉ ያበረታታል። ይህ አካሄድ ዘለበቱን ያደረገው ግለሰብ ጭንቀት ውስጥ ባልሆነበት ጊዜ ከሕግ አስከባሪ ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል። ይህም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የህግ አስከባሪዎች እገዛ ሊሰጡ እንደሚችሉ ለማሳየት ያስችላል። እንዲሁም በአካባቢው ውስጥ የሚኖሩ እና የኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አልዛይመር ያላቸውን ሰዎች ፖሊሶቹ ለይተው እንዲያውቁ ያግዛል። ይህ መተዋወቅ ለፖሊሱ እና ዘለበቱን ለአደረገው ሰው በጣም ጥቅም ይሰጣል።



- ✓ **ማሳወቅ።** እርስዎ ምቾት የሚሰማወት ከሆነ ሁኔታውን በተመለከተ ለጎረቤቶች ማሳወቅን እንመክራለን። አንዳንድ እንክብካቤ ሰጪዎች ስለ ጉዳዩ ለጎረቤቶቻቸው ማሳወቅ ምቾት እንደማይሰጣቸው እንረዳለን። ነገር ግን እነሱን በማሳወቅ የቤተሰብ አባልዎ ብቻቸውን ከአይን ሲሰወሩ/ ሲጠፉ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ እንዲቻል ይረዳል።። ጎረቤቶችዎ ወደ እርስዎ መደወል የሚችሉበትን የስልክ ቁጥር ወይም የቤተሰብዎ አባል እርዳታ ያስፈልገዋል ብለው ሲያስቡ ወደ 911 እንዲደውሉ ያስገንዝቡ።

- ✓ **የዋና ትምህርቶችን(Swim Lessons)** ግምት ውስጥ ያስገቡ። ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) ላላቸው ልጆች እንክብካቤ የሚሰጡ ሰዎች፣ አስቀድመው ልጆችዎ መዋኘት እንዲችሉ ማስተማር በርግጠኝነት ሕይወታቸውን ሊታደግ ይችላል!



# አገልግሎቶች

በአብዛኛው ጊዜ የሚመከሩ አገልግሎቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የስራ ክፍል ከፓዝ ፋይንደር ፎር ኦቲዝም (Pathfinders for Autism) ጋር በኦፊሰር ስልጠና፣ ለማሕበረሰብ  በመድረስ የማሳወቅ፣ ማህበረሰብን  በመወከል እረገድ  እና ለቤተሰቦች ቀጥተኛ አገልግሎት በመስጠት ዙሪያ በትብብር ይሰራል።

**ፓዝ ፋይንደርስ ለኦቲዘም /Pathfinders for Autism**
https://pathfindersforautism.org/

**ስፓኒሽኛ**
https://pathfindersforautism.org/articles/espanol/

**ፓዝ ፋይንደርስ ለኦቲዚም (Pathfinders for Autism) ከቤት መጥፋት እና አልመገኘት ሲከሰት ያሉ አገልግሎቶች**
https://pathfindersforautism.org/resources/safety/wandering-and-elopement/
**https://pathfindersforautism.org/መረጃዎች/ደህንነቱ/የመንቀሳቀስ-እና-መሽከርከር/**

**ዳውን ሲንድሮም ኔትወርክ ሞንትጎመሪ ካዉንቲ**
(Down Syndrome Network Montgomery County)https://dsnmc.org/

**ኦቲዝም ስፒክስ** (Autism Speaks)
www.autismspeaks.org/

**ሜሪላንድ ሎው ኢንተንሲቲ ሰርቪስ ግራንት ፔጅ (Maryland Low Intensity Services Grant page)**
**ሜሪላንድ የእድገት እክሎች**
https://health.maryland.gov/dda/Pages/liss.aspx

**ሞንትጎመሪ ካዉንቲ የአደጋ ጊዜ ማዕከል (Montgomery County Crisis Center)**
www.montgomerycountymd.gov/HHS-Program/Program.aspx?id=BHCS/BHCS24hrcrisiscenter-p204.html

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት**
**የአረጋውያን እና የአካል ጉዳት አገልግሎቶች**
www.montgomerycountymd.gov/HHS-Program/ADS/ADSADSResourceUnit-p179.html

**የአልዛይመር ማህበር**
(Alzheimer's Association)
www.alz.org/

ቤተሰቦቻቸው በእዚህ ችግር ስር የሆኑ የቤተሰብ አባላት ያሏቸው ቤተሰቦች የተለያየ ባህል እና ቋንቋ እንዳላቸው እንገነዘባለን። የእኛ የስራ ክፍል ሁሉም የማሕበረሰባችን አባላት ማለትም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ እና አጋር ድርጅቶች በዚህ አስቸጋሪ የሕይወት ጉዞ ውስጥ ብቻቸውን እንዳልሆኑ ለማረጋገጥ ይሰራል።

## ኤምሲፒዲ (MCPD)
## የኦቲዝም/አይዲዲ (IDD)
## የግንዛቤ ማስጨበጫ

በዚህ ተሽከርካሪ መኪና ውስጥ ኦቲዝም/አይዲዲ (IDD)ያለበት በጣም ጥሩ ሰው ሊኖር ይችላል። አደጋ በሚከሰት ጊዜ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የግላቭ ቦክሱን (glove box) ይፈትሹ። ሞንትጎመሪ ካዉንቲ ፖሊስ በኦቲዝም/አይዲዲ (IDD) ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እንዴት እንደሚደግፍ መረጃ ለማግኘት እባኮትን የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ፣

www.montgomerycountymd.gov/aidd

ሞንትጎመሪ ካውንቲ
የፖሊስ ዲፓርትመንት
(አፊሻል)

ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የደህንነት ማስተማሪያ ቲሸርቶች በሞንትጎመሪ ካዉንቲ ፖሊስ ህይወት ለማዳን እንዲያግዙ የተዘጋጁ ናቸው። ሰዎች ሲጠፉ እና አደገኛ ችግር ውስጥ ሲገቡ ብሎም እራሳቸውን ችለው መናገር በማይችሉበት ጊዜ እንደ አጋዥ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። ቲ ሸርቶቹ የኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) አካል ሲሆኑ የደህንነት መጠበቂያ ኪት (Wandering Safety Kit) ( ከስር በፎቶው ላይ እንደሚታየው) ከሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ መጠየቅ ይችላሉ፣
www.montgomerycountymd.gov/aidd
በተጨማሪም የፕሮግራም አስተባባሪው ጋር ኢሜይል መላክ ይችላሉ።




የኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የተሽከርካሪ መስኮት ላይ የሚለጠፍ ምልክት ክሊንግስ (Clings) የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) ከቤት የመጥፋት አደጋን የመከላከል ኪት አካል ሲሆኑ፣ የደህንነት መጠበቂያ ኪት (Wandering Safety Kit) ለማግኘት የሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ መጠየቅ ይችላሉ፣
www.montgomerycountymd.gov/aidd
በተጨማሪም የፕሮግራም አስተባባሪው ጋር ኢሜይል መላክ ይችላሉ።




የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የስራ ክፍል የደህንነት ኪት (safety kit) ያቀርባል፣ ይህም የደህንነት ከናቴራ እና ሌሎች መረጃዎችን ጨምሮ ከቤት የመጥፋትን ለመከላከል/ደሕንነትን የማስጠበቅ ጥረቶች እየሰራ የሚገኝ አካል ነው።
“በዚህ የሕይወት ጉዞ ላይ ብቻዎትን አይደሉም “ የሚል መልእክታችንን ለማስተላለፍ ነው።

**ለችግሩ ተጋላጭ ከሆነው**
**የማሕበረሰብ ክፍል**
**ጋር መገናኘት እና መገንዘብ።**



## ኦቲዝም/የአእምሮ
## እና የእድገት እክሎች
### ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወደ 911
### በሚደወልበት ጊዜ የሚጠቅም “ጽሁፍ/Script”

**ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለ 911 ይደውሉ!**

ከዚህ በታች ያለው የ 911 ፅሁፍ በግል እንክብካቤ የሚሰጡት ሰዎች በኩል ቀድሞ ሊሞላ ይገባል። ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም፣ እንክብካቤ የሚሰጡ ሰዎች ወደ 911 ሲደውሉ ለሚያናግራቸው ግለሰብ እና ፖሊሶች አስፈላጊ መረጃዎችን በቀላሉ ማስተላለፍ ይችላሉ።

ስም፡- ____________________

ትውልድ ቀን፡- ____________________

ቁመት፡-__________ ክብደት፡- __________

የፀጉር ቀለም ፡-__________አለርጂዎች ፡-፡ __________

የአይን ቀለም ፡-________የህመም አይነት፡- __________

መጨረሻ ለብሶ/ለብሳ የታየበት/የታየችበት ልብስ፡- __________

____________________

ማጋራት ከፈለጉ
የቅርብ ጊዜ ፎቶ እዚህ
ጋር ያስገቡ።

አጠቃላይ መግለጫ፣ ከዚህ በፊት ጠፍተው የተገኙበት ስፍራዎች (የቀድሞ መኖሪያ ቦታዎች፣ የሥራ ቦታዎች ወዘተ)

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________(እባኮትን ከጀርባው ይመልከቱ)

# ኦቲዝም/የአእምሮ
# እና የእድገት እክሎች
## ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወደ 911
## በሚደወልበት ጊዜ የሚጠቅም "ጽሁፍ/Script"

## ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለ 911 ይደውሉ!

ወደ 911 ወድያውኑ ይደውሉ፤ እኛ ቤተሰብዎን በፍጥነት ለማግኘት እንዲችሉ እናግዝዎታለን።

የቤተሰቤ አባል ከቤት ሲጠፉ የሚከተሉትን ባህሪያትን ያሳያሉ (በፍጥነት ሊንቀሳቀሱ እና ሊሮጡ ይችላሉ፤ ስማቸው ሲጠራ መልስ አይሰጡም፣ ወደ ውሃማ አካባቢዎች ይሄዳሉ፣ ወዘተ) ____________________

____________________________________________________________


የቤተሰቤ አባል ሲጠፉ ሊሄዱ የሚችሉባቸው ስፍራዎች (የአካባቢው ፓርክ፣ የአካባቢው የንግድ ስፍራዎች፣ውሃ አካባቢዎች፣ መዋኛዎች፣ ኩሬዎች ወዘተ) ____________________

እርስዎ ከልጁ ጋር ሲገናኙ ፖሊሶቹ የሚከተሉት መረጃዎችን ማወቃቸው ሊጠቅም ይችላል (በፍጥነት ሊንቀሳቀሱ እና ሊሮጡ ይችላል፤ ስማቸው ሲጠራ መልስ አይሰጡም፣ሊደበቁ ይችላሉ ወዘተ)______

____________________________________________________________

የቤተሰቡ አባል በተለይም ኦቲዝም ያለባቸው የቤተሰቡ አባላት ሊሄዱ የሚችሉባቸውን ስፍራዎች ፣ የውኃ ቦታዎች ለይቶ ማወቅና ለአደጋው ምላሽ ለሚሰጡ ፖሊሶች መንገር በጣም ጠቃሚ ነው። እባኮትን ለ 911 የስልክ ጥሪ ካዘጋጁት ጽሁፍ ጋር የጎግል ካርታ ያትሙ እና በቤትዎ ዙሪያ ያለውን አካባቢ ያክበቡ እና አደጋኛ ስፍራዎችን እና የቤተሰብዎ አባል ከቤት በሚጠፉበት ጊዜ ሊሄዱ የሚችሉባቸው ስፍራዎች ለይተው ምልክት ያድርጉ።

ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌያዊ ካርታ ይመልከቱ፡-




A = ቤታችን
(12345 የመንገድ ስም)

★ = ሊገኙባቸው
የሚችሉባቸው ስፍራዎች

የግለሰቡን እና የሕመም ሁኔታ ማወቅ እና መገንዘብ

እነሱን በፍጥነት እና በደህና ሁኔታ ወደ ቤት ለማምጣት ያግዛል።



# አልዛይመር/ዴመንሽያ (Alzheimers/Dementia)
## ለጎረቤት የሚሰጥ ደብዳቤ

እባክዎትን ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ግለሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ይተባበሩን፡-

ስም፡- ____________________________________________________________

## አልዛይመር /ዴመንሽያ አለበት።

ይህ ደብዳቤ ጎረቤቶችዎ ባልተለመደ ሰዓት ልጅዎን ብቻውን / ብቻዋን ሲያዩ፣ ወደ እርስዎ የእጅ ስልክ ላይ ወይም ወደ 911 እንዲደውሉ ያስችላቸዋል።

የትውልድ ቀን፡- ____________________________

ቁመት፡- ______________ ክብደት፡-______________

የፀጉር ቀለም ፡- ________የአይን ቀለም ፡-______________

አለርጂ ፡- ____________________________

ብዙ ጊዜ የሚለብሱት የልብስ አይነት፡-______________

____________________________________________

ማጋራት ከፈለጉ
የቅርብ ጊዜ ፎቶ እዚህ
ጋር ያስገቡ።

____________________________________________________________

እሱ/እሷ ብዙውን ጊዜ ብቻውን/ብቻዋን ወደ ውጪ አይወጣም/አትወጣም፣ እሱን/እሷን ካየኸው/ካየሀት እባክዎትን ቀርበው ለማናገር እንዳያመነቱ። እባክዎትን ልጄን ብቻውን ሆኖ ከተመለከቱት ወደ የእጅ ስልኬ ይደውሉልኝ።

እኛ በተቻለን አቅም ሁል ጊዜ እንከታተለዋለን/ እንከታተላታለን፣ አንዳንድ ጊዜ ግን እኛ ሳናውቅ ይወጣል/ትወጣለች እና ግራ ይጋባል/ትጋባለች።

ለማጋራት የሚፈልጉት ተጨማሪ መረጃ ካለ ለኛ ያጋሩን። እናመሰግናለን።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ስም፡- ____________________________________________________________

አድራሻ ፣ ____________________________________________________________

ስልክ(ዎች): ____________________________________________________________

# እውቅና በመስጠት ግንዛቤን ማዳበር



▲ ጆን እና ቤተሰቡ በ 2015 የኤምሲፒዲ (MCPD) ኦቲዝም ምሽት ዝግጅት ላይ የኤምሲፒዲ ዋና የስራ ሀላፊነትን ሽልማት (MCPD Chiefs' Award) ሲቀበል።



▲ የኤምሲፒዲ (MCPD) ኦፊሰር ኬቪን ኮሬአ እና አባቱ ማኑኤል።




የመጀመሪያ ገጽ፣ ጃክ የ 2015 ዓመታዊ የኦቲዝም የምሽት ዝግጅት ላይ
ንግግሩ ካደረገ በኋላ እናቱን ሲያቅፍ። ጄክ የመጀመሪያው እና የአሁኑ የኤምሲፒዲ (MCPD) ኦቲዝም አምባሳደር ነው።
ከግራ ጀምሮ፣ የኤምሲፒዲ ዋና ማኔጀር፣ የፖሊስ ኦፊሰር ሎሪ ሬየስ እና ጄክ።



# ኦቲዝም/የአእምሮ እና የእድገት እክሎች

## ለጎረቤት የሚሰጥ ደብዳቤ

### እባክዎትን የልጃችንን ደህንነት ለመጠበቅ ይተባበሩን:-

ስም:- ______________________________

### ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD)/አለበት/አለባት

ማጋራት ከፈለጉ የቅርብ ጊዜ ፎቶ እዚህ ጋር ያስገቡ።

እሱ/እሷ ______________ ዓመት ዕድሜ ነው/ናት።

እኛ ልጃችንን በጥንቃቄ እንጠብቃለን፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደ ሌላ ስፍራ ይሄዳል/ትሄዳለች።.

ልጃችንን ብቻውን/ብቻዋን ካዩት/ካይዋት እባክዎትን ይደውሉልን

______________________________

እኛም እየፈለግነው/እየፈለግናት ነው የሚሆነው። ከላይ ባለው ቁጥር እኛን ማግኘት ካልቻሉ፣ እባኮትን ወደ 911 ይደውሉ እና ልጃችንን እንዳገኙ ይንገሯቸው።

______________________________ በደንብ መናገር አይችልም/አትችልም።

ልጃችን አደጋን ይፈራል/ትፈራለች።እርሱ/እሷ ወደ ውሻ ሊቀርብ/ልትቀርብ ይችላል/ትችላለች ወይም በደንብ ሳያይ/ሳታይወደ መንገድ ውስጥ ሊገባ/ልትገባ ይችላል/ትችላለች። የቤትዎ በር ክፍት ከሆነ ወደ ቤትዎ ሊገባ/ልትገባ ይችላል/ትችላለች።

______________________________ በቀላሉ ይጠፋሉ እናም መጥፋታቸውን አያውቁም። ልጃችንን ጥያቄ ቢጠይቁ መልስ ላይሰጥዎት/ላትሰጥዎት ይችላል/ትችላለች

______________________________ መስማት የማይችል/የማትችል መስሎ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን ልጃችን ማዳመጥ ይችላል/ትትላለች። ነገር ግን የሚሰማውን/የምትሰማውን ወይም የሚያየውን/የምታየውን አይረዳም/አትረዳም ወይም አያደርግም/አታደርግም። እናመሰግናለን።

ስም:- ______________________________

አድራሻ ፣ ______________________________

ስልክ(ዎች): ______________________________

ስለ ኦቲዝም ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት ይህን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ። www.pathfindersforalzheimers.org

ስለ ዳውን ሲንድረም ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት ይህን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ። www.DSNMC.org

ይህ ሰነድ በፒዲኤፍ (PDF) ከዚህ በታች ባለው ሳይት (site) ውስጥ ይገኛል።ይህ መረጃ ለእርስዎ ቤተሰብ በሚስማማ መልኩ ሊስተካከል ይችላል። www.montgomerycountymd.gov/aidd


# የግንዛቤ ማስጨበጫ በተግባር




ኤምሲፒዲ (MCPD) ከፓዝፋይንደር ፎር ኦቲዝም (Pathfinders for Autism) ጋር በመተባበር የትራፊክ ማስቆም ምሳሌያዊ ልምምድ ስልጠና እና በአካል የልምምድ ፕሮግራም ይሰጣል።ቀጣይ ያሉ ቀናትን ለማወቅ እዚህ ክሊክ (click) ያድርጉ https://pathfindersforautism.org/




የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የስራ ክፍል ፖሊሶች በትምህርት ቤት ወስጥ በማሕበረሰብ ድህንነት ዙሪያ ሲያስተምሩ።




የኤምሲፒዲ ኦቲዝም/አይዲዲ(IDD) የስራ ክፍል ፖሊሶች እና አጋር ድርጅቶች ማሕበረሰብን የመድረስ ስራ ሲያከናውኑ።



# አልዛይመር/ዴመንሽያ (Alzheimers/Dementia)

## ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወደ 911 በሚደወልበት ጊዜ የሚጠቅም “ጽሁፍ/Script”

ከዚህ በታች ያለው የ 911 ፅሁፍ በግል እንክብካቤ የሚሰጡት ሰዎች በኩል ቀድሞ ሊሞላ ይገባል። ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም፣ እንክብካቤ የሚሰጡ ሰዎች ወደ 911 ሲደውሉ ለሚያናግራቸው ግለሰብ እና ፖሊሶች አስፈላጊ መረጃዎችን በቀላሉ ማስተላለፍ ይችላሉ።

**ከቤት መጥፋት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለ 911 ይደውሉ!**

ስም:- ______________________________

ትውልድ ቀን:- ______________________________

ቁመት:- ____________________ ክብደት:- ____________________

የፀጉር ቀለም :- ____________ አለርጂ :- ______________________

የአይን ቀለም :- __________ የህመም አይነት:- ____________________

መጨረሻ ለብሶ/ለብሳ የታየበት/የታየችበት ልብስ:- ____________________

ማጋራት ከፈለጉ የቅርብ ጊዜ ፎቶ እዚህ ጋር ያስገቡ።

አጠቃላይ መግለጫ፣ ከዚህ በፊት ጠፍተው የተገኙበት ስፍራዎች (የቀድሞ መኖሪያ ቦታዎች፣ የሥራ ቦታዎች ወዘተ)

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________ (አባኮትን ከጀርባው ይመልከቱ)